አርጎባ ጀነርት

የአርጎባ ልማት ማህበር

Argoba Development Association



ሱልጣን መሀመድ አሸራፌ



ማውጫ ገፅ

1.መልዕክት በአርገባ ልማት ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ ----------1

2.መልዕክት በአርገባ ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ----------2

3.የሱልጣን መሀመድ አሸራዩ አጭር ሕይወት ታሪክ ----------3

4.የዲያስፖራዎች ገፅ:-ጥቂት ቆይታ ከዋናው አስተባባሪ ጋር ----------4

5.በዘመን ተሻጋሪና ቅብብሹሽ የታሪክ ዕሴቶቻቸው የሚታወቁ የኢትዮጵያ

ፈርጦች ----------10

6. የአርገባ ቅርሶች----------16

ዋና አዘጋጅ

እስማኤል ጡሀ

አዘጋጅ

ተማም ሲራጅ

አርትኦት

ናሆም ፍቅሩ

የአርጎባ ልማት ማህበርን መደገፍ እና መርዳት ለምትፈልጉ

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ቁጥር

CBE 1000005845797

አድራሻ:- ዋና ሚስሪያ ቤት አዲስ አበባ ሜክሲኮ ማይጨው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ

Email. argobadevassoc@gmail.com

ስልክ 251 911 87 88 54

+251 911 80 89 95

መልዕክት በአርጎባ ልማት ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ



አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱሏሂ ወበረካቱሁ

ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም ፤የተከበራችሁ የአርጎባ ህዝብ እንደሚታወቀው የአርጎባ ህዝብ እጅግ ውጣ ውረድ ከበዛው ፈተናና መከራ ከሞላው ታሪኩ እና በዚህም ታሪኩ ውስጥ ካሳየው ጅግንነትና ከከፈለው መስዋእትነት ጋር በማይመጥን የእውቀት እና የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ መገኘቱ እጅግ የሚያንገበግበው ትውልድ በተናጠልም ሆነ በተቀናጀ መልኩ የተለያዩ ጥረቶች ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም የሚፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት አልቻለም።

በመሆኑም ቀደምት አያቶቻችን በአርጎባ ህዝብ አንድነት እና ጀግንነት መለዮ ዙሪያ የገነቡትን አርጎባዊ ፍቅርና ስሜት በመውረስ ይህ ስሜት የቆመበትን ኋላ ቀር ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መሰረት በመለወጥ የአርጎባን ህዝብ ዙሪያ መለስ ጥቅሞች በላቀ ደረጃ እንዲከበሩ ለማስቻል ከጥቅምት 15/2015 ዓ.ም. ጀምሮ የአርጎባ ልማት ማህበር በአዲስ መልክ በተለያዩ ዘርፎች እየተንቀሳቀሰ ሲሆን ከነዚህም አንዱ ከ450 አመታት በፊት ተቋርጦ የነበረውን የይፋት ወላስማ ሱልጣኔት ሱልጣን ለማስቀጠል በአፋር ክልል አርጎባ ልዩ ወረዳ ጋቾኔ ከተማ የሚያካሂደውየሱልጣን በዓለ ሲመት ፕሮግራም ነው። የአርጎባ ማህበረሰብ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ በሀረር ክልሎች በስፋት የሚገኝ ሲሆን በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ተሰራጭቶ የሚኖር ማህበረሰብ ነው።

ዛሬ በዚህ እጅግ ታሪካዊና ለትውልድ ተሻጋሪ በሆነ በዓለ ሲመት ላይ ለመታደም ጥሪያችንን አክብራችሁ ከሁሉም አካባቢዎች እና ከውጭ ሐገር የመጣችሁ ወንድም፣ እህቶቻችን፣ አባት እናቶቻችን እንኳን በሰላም መጣችሁ እላለሁ።

የአርጎባ ልማት ማህበር በተለያዩ ክልሎች የሚኖረውን የብሔረሰቡን ተወላጆች በባህል፣በቋንቋ፣ በታሪክና በማንነት ልማት በማሳተፍ እንዲሁም ከኢኮኖሚያዊና ከማህበራዊ ችግሮች ተላቀው የአርጎባ ህዝብ ዙሪያ መለስ ጥቅሞች በላቀ ደረጃ እንዲከበሩ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል።

ሰፊ ራዕይ ይዞ የተነሳው የአርጎባ ልማት ማህበር ራዕዩን ከግብ ለማድረስ ከተለያዩ አጋር አካላት ድጋፍ አስፈላጊ በመሆኑ ማገዝ ከሚፈልግ ማንኛውም አካል ጋር በጋራ ለመስራት ፍላጎታችንን እና ዝግጅታችንን እየገለፅን በበዓለ ሲመቱ ላይ የሚኖራችሁ ቆይታ የተሳካና ያማረ እንዲሆን እመኛለሁ! አመሰግናለሁ።

የአርጎባ ልማት ማህበር
የቦርድ ሰብሳቢ
አቶ መሀመድ ሙሳ አበጋዝ

የአርጎባ ልዩ ወረዳ አስተዳደር መልዕክት
አቶ ባጣ አቦ



የአርጎባ ልዩ ወረዳ ከ1989 ዓ.ም. ጀምሮ 13 ቀበሌዎች ያሉት ሲሆን ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን በርካታ የልማት ስራዎችን ማከናወን ተችሏል።የአርጎባ የይፋት ወላስማ ሱልጣኔት በዓለ ሲመት በአርጎባ ልዩ ወረዳ ጋቾኔ ከተማ ለሚካሄደው: በዓለ ሲመት እንደ አርጎባ ልዩ ወረዳ የመንግስት አካል የተለያዩ ዝግጅቶችን አድርገናል:: በወረዳችን የይፋት ወላስማ ስርወ መንግስት ሱልጣኔት ሹመት ላይ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት፤የአርጎባ ማህበረሰብ ከሚኖርባቸው ከተለያዩ ክፍሎች ብሎም ከውጭ ሀገራት ተሳታፊ ለሚሆኑ ታዳሚዎች ከፍተኛ ዝግጅት ተደርጓል::

በዓለ ሲመቱን ለመታደም የሚመጡ እንግዶች ሰላማቸው በተጠበቀ መንገድ ፕሮግራሙ እንዲካሄድ ከአርጎባ ልማት ማህበር አመራሮች ጋር በመሆን የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተሰርተዋል::

የአርጎባ ይፋት ወላስማ ሱልጣኔትን ስናስቀጥል በተለያዩ አካባቢዎች ተበትነው የሚኖሩ ወገኖቻችን አንድነት የሚያጠናክር እንዲሁም ቋንቋችንን፣ ባህላችንን እና፣ታሪካችንን አጉልተን የምናወጣበትን እድል ስለሚፈጥርልን ሱልጣኔቱን ማስቀጠላችን ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው::

በበዓለ ሲመቱ ላይ ለበርካታ አመታት ተራርቀው የነበሩ የማህረሰቡ አባለት የሚገናኙበት የአርጎባ ልዩ ወረዳንም አሁናዊ ሁኔታ የሚመለከቱበት ሲሆን በፕሮግራሙም ላይ በመገኘታቸው ለወረዳው ቀጣይ ትልም እና እቅድ ትልቅ ጥቅም አለው::

በመጨረሻም ለአርጎባ ይፋት ወላስማ ሱልጣኔት በዓለ ሲመት ላይ የሚሳተፉ የማህበረሰቡ ተወላጆች፣ከፍተኛ አመራሮች፣ባለሀብቶች የሚገኙ ሲሆን የአርጎባ ልዩ ወረዳ ህዝብ የእካባቢያቸውን ሰላም በማስጠበቅ የእንግዶቻችን ምቾት እና ሰላማቸው ተጠብቆ የአርጎባ ማህበረሰብ የሚታወቅበትን የእንግዳ ተቀባይነቱን ባህል አጉልቶ የሚያሳይበት እንደሚሆን በማመን ሁሉንም አካላት እንኳን ለበዓለ ሲመቱ መርሐግብር አደረሳችሁ እላለሁ።

የሱልጣን መሀመድ አሸራዩ አጭር የሕይወት ታሪክ



መሐመድ አሸራዬ መሐመድ ከእናታችው አይከድጅ ግራዝማች ያሲን ሷሊህ እና ከአባታችው አሸራዬ መሐመድ በ1966 ዓ.ም. ታህሳስ ወር ላይ በአፋር ክልል አርጎባ ልዩ ወረዳ ታች-መጠቅለያ ቀበሌ ልዩ ስሙ ገርባ የሚባል ጎጥ ላይ ተወለዱ:: ከመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸው ቤተሰቦች የተወለዱ ሲሆን ወላጆቻቸው በግብርና እና በከብት እርባታ ኑሯቸውን ይመሩ ነበር:: :: ከልጅነት እስከ እድገት በዚሁ በታች-መጠቅለያ የቆዩ ሲሆን በ1989 ዓ.ም. ትዳር መሰርተው የ4 ወንድ ልጆች እና የ2 ሴት ልጆች አባት ለመሆን ችለዋል::

የስራ ኃላፊነትን በተመለከተ በተለያዩ ወቅቶች የህዝብ ኃላፊነትን በመቀበል ህዝቡን ሲያገለግሉ ቆይተዋል :: ከ1994 ዓ.ም. እስከ 2000 ዓ.ም. በአርጎባ ልዩ ወረዳ በተለያዩ በጤና ፣በማህበረሰብ በአስተዳደር በመሳሰሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች በኃላፊነት አገልግለዋል :: በተጨማሪ ለ3 አመታት የአርጎባ ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳደር በመሆን የአርጎባን ማህበረሰብ በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግሉም የቆዩ ... ቆይተዋል :: በ1997 ዓ.ም. በምርጫ ተወዳድረው በማለፍ ለአፋር ብሔራዊ የክልል ምክር ቤት አባል በመሆን ለአምስት አመት እና በ2002 ዓ.ም. ምርጫ የአርጎባ ህዝብ በድጋሚ መርጧቸው ለተከታታይ አስር አመታት የህዝብ ልሳን እና አንደበት በመሆን አገልግለዋል::ከዚህም በተጨማሪ ለአርጎባ እና ለኖሩበት ማህበረሰብ የአገር ሽማግሌ በመሆን ብዙ ጉዳዮች ሰላማዊ እልባት እንዲያገኙ የበኩላቸውን አሻራ አሳርፈዋል።

በአሁኑ ሰአት በኮንስትራክሽን ዘርፍ በመሰማራት ከአርጎባ ልዩ ወረዳ ባለፈ በሌሎች ወረዳዎች ላይ በበርካታ የልማት ስራዎችን ላይ በመሳተፍ የግል ስራቸውን በመስራት ላይ ይገኛሉ::

ጥቂት ቆይታ ከዋናው አስተባባሪ ጋር



አርነባ ጀበርት፤- ስም እና ኃላፊነቶን ቢነግሩን ?

አቶ ሰይዱ፡- ሰይዱ ኑሩ መሀመድ እባላለሁ፣የሰራ ኃላፊነቴ ከሀገር ውጪ ያሉ የአርነባ ማህበረሰብ ዲያስፖራዎችን በመወከል የሀገር ውስጥ አስተባባሪ ነኝ ።

አርነባ ጀበርት፤-ይሔ የምትንቀሳቀሱበት ድርጅት ወይም ግሩፕ ስያሜ ካለው እና መቼ እንደተመሰረተ ቢገልፁልን ?

አቶ ሰይዱ፡- ድርጅት ሳይሆን ግሩፕ ነው በዋትስኧፕ የግሩፕ ስሙ 'የተቸገሩትን እንርዳ ነው' የሚለው ።ይሔም የተጀመረው በረመዳን ወር በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2012 ዓ.ም. ሚያዚያ ወር ላይ ነው ።እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረ ሶስት አመት ሆኖታል።

አርነባ ጀበርት፤- ይሄንን እንቅስቃሴ ለመጀመር ምን አነሳሳችሁ?

አቶ ሰይዱ፡- ወቅቱ የኮሺድ ሰዐት ነበር በኮሺድ ሰዐት ሁሉም እያንዳንዱ ህብረተሰብ በአካባቢው አሜሪካ ላይ ተደራጅቶ የአካባቢውን ሰው ሲረዳ ነበር። ሀረር ያሉት ሀረር አካባቢ የደቡበቹም እንደዛው ሁሉም ተደራጅቶ የአካባቢውን ሰዎች ሲረዳ ነበር። ለምን አብዛኛውን ትኩረት ያደረጉት ክፍለ ሀገሮችን ነበር ። በተለይ ትንንሽ ከተሞች ላይ ነው ትኩረት ያደረጉት ።አብዛኛዎቹ ያው ጉሊት ወጥተው ብዛት ያላቸው ሰዎች የሚሠበሠቡበት ቦታ ስለቀረ ከቤት ውጪ ወጥተው ስራ የሚሰሩ ሰዎች ላይ ነው ትኩረት ያደረጉት። እንግዲህ የተሰባሰብንበት አንዱ ምክንያት ይህ ነበር። ሌላው እኔም በራሴ አርነባ ነኝ። የአርነባ ማህበረሰብ ያው ብዙ ጊዜ በከተማ ውስጥ ሳይሆን በብዛት ያለው ወደ ገጠር አካባቢ ነው። ገጠር ውስጥም ሆነው ከተወሰነ ብሔር ጋር ነው የሚኖሩት እንጂ ከተማ ውስጥ ብዙም አይኖሩም ።አዋሽ እና አዳማ አካባቢ ካልሆነ በስተቀር ወደ ገጠር ነው የሚበዙት እና ስለዚህ 'እነሱንስ ማን ይረዳቸዋል?' ለምን ያው በጉሊት ስራ የሚተዳደሩ እና አግብተው የፈቱ ልጅ ያላቸው ስለነበሩ በወቅቱ በነበረው ከኮሺድ ወረረሽኝ ጋር በተያያዘ የሰዎች መሰብሰብ የተከለከለበት ጊዜ ስለነበር እነሱ ቀን በቀን የሚያገኙት ወይም በሳምንትም አንዴ የሚያገኙት ገቢ ስለሚቀርባቸው ይህን ታሳቢ በማድረግ 'ለምንድን ነው ከሀገር ውጭ ያለን ዲያስፖራዎች ወገኖቻችንን አሰባስበን በሀገር ውስጥ ያሉትን ተጎጂ ማህበረሰቦች የማንረዳው?' በማለት ነው የተሰባሰብነው ።ይሄን አስቤ፤ ዘመድ እህት ወንድሞች አሉኝ ከነሱ ነው የጀመርኩት እና ከሁሉም ጋር አወራን ያለውን ነገር ነገርኳቸው። 'ይሔን የኛ ህዝብ የሚረዳው የለም አንድ እና

ጥቂት ቆይታ ከዋናው አስተባባሪ ጋር

...የቀጠለ

አንድ የሚያውቀው አርጎባን ነው ካልሆነ አፋርን ወይም አማራን ነው ሌላው ሁሉ የራሱን አካባቢ ብቻ ነው የሚረዳው' በማለት ያው እየደዋወልኩ አሜሪካም፣ አውስትራሊያም ካናዳም እንደዛው ዘመዶች ስላሉኝ ለነሱ ነገርኳቸው ። ሁሉም 'የራሳችንን ድርሻ እና ኃላፊነት መወጣት አለብን' በማለት ሁሉም በሞራል መንቀሳቀስ ጀመረ።እንደዛውም ደግሞ ከሌላ ብሔር የሆኑ ጓደኞቻችን አሉ። እነሱንም በመጠየቅ ይኼ ነገር ተጀመረ ማለት ነው። ስለዚህ ያው ጅምሩ ይህን ይመስላል። ቀጣዩ ዙር ደግሞ 'በምን መልኩ ነው ይሄንን ነገር መርዳት ያለብን?' የሚለውን ደግሞ ተወያይተንበት። በውይይቱ 'በምንድን ነው? በብር ነው? ወይስ በዓይነት ነው የምንረዳው?' የሚለውን ነገር ደግሞ አጥንተን 'በዘይት እና በዱቄት መስጠቱ ይሻላል' ተብሎ በዛው ተወስኖ ነው የተገባበት እና ሌላ ደግሞ አሁን አውሮፓ ያሉ ዲያስፖራዎች ላልሰሙት ለሌሎች ሰዎች በማሰማት ፣ሳኡዲ እንዲሁም ዱባይ ላይ ያሉ ዜጎችም ጉዳዩን ከሰሙ በኋላ ብዙ ሚና ተጫውተዋል። እንግዲህ ይሄንን በማሰባሰብ ነው በመጀመሪያውን ዙር ማህበረሰቡን ወደ መርዳት የገባነው።

አርጎባ ጀበርት፤- በዚሁ የእርዳታ እንቅስቃሴ ውስጥ ምን ያክል የዲያስፖራ አባላት ተሳትፎ አድርገዋል?

አቶ ሰይዴ፣ ቅድም እንዳልኩህ ከአውሮፓ፣ አውስትራሊያ፣ከአሜሪካ፣ከካናዳ፣ ከዱባይ፣ከሳኡዲ እና የተወሰኑት ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ዲያስፖራዎች አንድ ላይ ወደ ስምንት መቶ ይሆናሉ ድጋፍ ያደረጉት ። አብዛኛውን ድጋፍ ያደረጉት አሜሪካ ነው ብዛትም አላቸው። በኢኮኖሚም የተሻሉ ስለሆነ ማለት ነው።

አርጎባ ጀበርት፤- ወደ እርዳታው ስንገባ በምን ያክል ዙር ምን ያክል ሰው ረዳችሁ?



ጥቂት ቆይታ ከዋናው አስተባባሪ ጋር

...የቀጠለ

አቶ ሰይዴ፡- በመጀመሪያው ዙር ብር ወደ ማሰባሰብ ነው የገባነው።ገንዘብ ካሰባሰብን በኋላ የመጀመሪያ ዓመት ላይ ወደ 9,920 ሰው ነው የረዳነው ።እርዳታ ያደረግነውም ሰባት የተለያዩ አካባቢዎች ነው።

አርነባ ጀበርት፤- በየዙሩ ምን ያክል ሰው ረዳችሁ ?መጥቀስ ከተቻለ?

አቶ ሰይዴ ፡- ትኩረት ያደረግንባቸው ቦታዎች ነበሩ ለምሳሌ፡- አልዩ አንባ 1,500 ሰው ነው የረዳነው፣አፋር ክልል አርነባ ልዩ ወረዳ ወደ 1,660 ሰው ነው። እንደዚ እያልን እየቀጠልን ሸዋሮቢትም ወደ 2,500 ሰው ረድተናል።



አርነባ ጀበርት፤- በአጠቃላይ በሁሉም ዙሮች ምን ያክል ሰው ረድታችኋል?

አቶ ሰይድ :- 9,920 ሰው ረድተናል።

አርነባ ጀበርት፤- ይሔኛው በ2012 ዓ.ም. ነው ማለት ነው?

አቶ ሰይዴ፤- አዎ

አርነባ ጀበርት፤- በ2013 እና በ2014 ዓ.ም. የረዳችሁትን የሰው ቁጥር ቢነግሩን?

አቶ ሰይዴ፡-ከዛ በፊት የመጀመሪያው አመት ላይ ማህበረሰቡን ስንረዳ የነበረው በዘይት እና በዱቄት ነበር ፣ በሁለተኛው አመት ላይ ያው ኮቪድም በመቀነስ ላይ ስለነበር ከ3,000 ሰው በላይ የተረዳ ሲሆን የድጋፍ መጠኑም ስለቀነሰ እንዲሁም የሚገዙ እቃዎች ዋጋ ስለጨመረ ድጋፉን ያደርግነው በገንዘብ ነበር።


Argoba Diaspora Community and Partners

1.				
2.				
3.				
4.				
5.				
6.				
	Overall Total ⟶			

አርነባ ጀበርት፤- በሶተኛው ዓመትስ?

አቶ ሰይዴ ፡- በሶተኛው ዓመት ላይ ያለው ትንሽ ቁጥር ያለው ሰውም የራሱ ፕሮግራም ላይ ስለነበር የሚመጣውም ብር እንደዚያው እያነሰ የመጣበት ነበር። ይህም እርዳታ የቀነሰበት ምክንያት የሚረዱት ዲያስፖራ አባላት ካለቻቸው ለፍተው ካመጡት ላይ እየረዱ ስለነበረ ነው። ያንን ደግሞ ሲያወጡ ለታለመለት አላማ በአግባቡ መዋል አለበት።

ትርፏው ላይሆን ባለን አቅም ጠየዋቹን እንርዳ ብለው ነው የሚልኩት አዚህ ስንመጣ ያሰቡት ማከፋፈል ላይ ችግር ነበር። በመጀመሪያው አመት ላይ አልሀምዱሊላህ ከጠቅ ጥርስነት ሀሳ ጥርስነቱ ተከፋፍሏል። በዚህ መሀል አቅም ሊላቸውን ሰዎች ለመርዳት ብለው መጥተው እርዳታው በሚሠጥበት ጊዜ የሚሰርቁ ነበሩ። እርዳታው ተደራሽ እንዳይሆን የሚያደርጉ ነበሩ። ውጪ ያሉት ጀማሞ ይሄን በሚሰሙበት ጊዜ 'እናንተ ዘመድ የላችሁም እንዴ?' ይባላሉ 'ለዘመዶቻችሁ ለምን አትረዱም?' ይባላሉ። ምክንያቱም የሚላከው እርዳታ በትክክል ካልደረሰ፣ አይታሸ ጀማሞ ሌላ ጥቅም የሚፈልግ ከሆነ ጥያቄ ስለሚያስነሳ እነዚህ ነገሮች የተመሰኑ ችግሮች ፈጥረዋል። በጀነብ የተደራጀን ከሆንን በኋላ የምንቀጥልበት ሁኔታ አለ እኛ ሁኔታው ይሐሄን ይመስለል።

ቀለርነባ ጀበርቅ፤ በዘንድሮ አመት በ2015 ዓ.ም. እርዳታው እንደተቋረጠ አሜሁተውቸል የቆመበት ምክንያት ምንድን ነው? እንደገናም ወደፊት ከአስካሁኖቹ ከነበረው በተሸለ መልኩ ምን ለመስራት አስበቸኋል?

አቶ ሰይዲ፤ መቋረጥ አይባልም ያው ለጊዜው አቁመነዋል። ይሄንንም በጊዜያዊነት ያቆምንበት ምክንያት አገር ውስጥ እኔ እኛ የተወሰንን ሰዎች ብቻ ነው የምንቀሳቀሰው። ይሄንን ነገር ለሚመለከተው አካል ለማድረስ በየቦታው ፊሱን የቻለ ማፋጥ ወይም ማህበር ያስፈልጋል። ካልሆነም ግለሰት ያለው ሰው በትክክል ታማኝ መሆን ይኖርበታል።





ስለዚህ በማንቸውም ግዜ እርዳታ በምንልክበት ለዓት ለውየው 1,000 ብር ለጥቱነው በጣም ለተቸገፉት መርጠህ አድርስ ሲባል የሚሰጠው 500 ብር ሊሆን ይቸላል። ያም ጀማሞ ለአንዲ ይሰጥ እኖ ለዘመዲ ካልሆነም የፊሱን ሰው የማከቱት ሁኔታ አለ። ስለዚህ እንደዚ ዓይነት ነገሮችን ዲያስቆፊው ምን ያክል ለጭት እንደሚያመጣው እኖውቃለን።ከመንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶቸ የሚመጣ ገንዘብ አይደለም አንድኖ አንድ ከቸው አርነባ ከሆኑ ልጆቸ የሚመጣ ብር ነው።

ጥቂት ቆይታ ከዋናው አስተባባሪ ጋር

...የቀጠለ

ሌላ ምንም ሚስጥር የለውም። ይሔን ገንዘብ ደግሞ እንደዛ ለፍተው አምጥተው ለሚመለከተው ወይም ለሚገባው አካል ካልተሰጠ ተጠያቂ የምሆነው እና ያለሁት እኔ ነኝ ። አሁን ላይ ግን የተወሰኑ በጣም ጠንካራ የሆኑ ሰዎችን አግኝቻለው ። ሸዋሮቢትም አካባቢ የተወሰኑ እንዲሁም ሶስት እና አራት ቦታዎችም የሚያግዙንን ሰዎች አግኝተናል። ለወደፊት ግን ከዚህ በበለጠ ከዲያስፖራው አቅም ያላቸው እና የተማሩ የኛ ሠዎች በጣም በብዛት አሉ።ከነዚህ ውስጥ እርዳታ ማድረግ የሚፈልጉትን ፈልገን የሆስፒታል ማቴሪያል ድጋፍ እንዲሁም ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለመጥቀስ ያህል ለህዝብ ውሀ ማውጣትም ሆነ ትምህርት ቤት ለመገንባት በትልቁ እና በሠፊው እቅድ የምንይዝበት ሁኔታ አለ። ስለዚህ በቀጣይ በሰፊው ወደ ስራ እንገባለን።

አርጎባ ጀበርት፤- በርካታ እቅዶች እንዳላችሁ ገልፃችኋል። ከገንዘቡም ከእርዳታውም በዘለለ ትላልቅ ነገሮች የተቸገሩ አካባቢዎች ለመርዳት እና ለማቋቋም እንዳሰባችሁ ገልፀውልኛል። ይሄን ለማድረግ ከማን ምን ይጠበቃል?

ቆ ሰይዲ፣ አንደኛ ከማህበረሰቡ ነው። እነዚህ አሁን ያልኳቸው ነገሮች በአካባቢያቸው በሚተገበሩበት ግዜ ማህበረሰቡ በአግባቡ መጠቀም አለበት ።የሚሰሩ ነገሮች እንዳይበላሹ እና ደግሞ ብዙ ዓመት እንዲጠቀሙበት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር እንዲሁም ስራዎች ሲሰሩ በጉልበት እና በአስተያየት ድጋፍ በመስጠት ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።ከመንግስት አካልም ደግሞ ምንም ዓይነት ቢሮክራሲ ሳያበዙ ለስራ እና ለግንባታ የሚያስፈልገውን ቦታም ይሁን ሌሎች የሚያስፈልጉ ነገሮችን ቶሎ ጨርሰው ማስረከብ አለባቸው ""ይሄን ከነሱ እንጠብቃለን። ከዲያስፖራው ደግሞ ይሄን ሲያይ ያወጣው ገንዘብ 'ምን ላይ ነው የዋለው?' ማለት አለበት። እንዳልኩህ ይሄ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አይደለም። የኛው ወገኖቻችን ናቸው እርዳታ የሚያደርጉት ያወጡትን ነገር ማየት ይፈልጋሉ መርዳት ይፈልጋሉ። ስለዚህ ከዲያስፖራውም ያልተሳተፉም አሉ። መሆኑም ይሔ ግሩፕ ዋና አላማው ወገኖቻችንን እንርዳ ነው ካልረዳን ማነው የሚረዳን? ሁሉም የራሱን ነው የሚረዳው አካባቢውን አልምቷል።

እስካሁን ያልለማ አካባቢ ቢኖር የኛ አካባቢ ነው። ስለዚህ ዲያስፖራው ይሄንን ታሳቢ በማድረግ ከጎናችን መቆም አለበት። ከዲያስፖራው የሚያስፈልጉ ብዙ ነገሮች አሉ። አንዱ አንዱን ለማስታወስ እወዳለሁ። የሚችለውን ያህል በብር እንኳን ባይችል በአስተያየት ፣በሞያው መርዳት አለበት። ስለዚህ ሁላችንም ወገኖቻችንን እንርዳ ለራሳችን በፈጣሪም ዘንድ ትልቅ ነገር ነው። ታሪክ እንስራ ብዙ አመት ወደኋላ ቀርተናል። አሁን ወደፊት መሔድ ነው ።እኛ በህይወት ያለን ሰዎች የምንችለውን ያህል ድጋፍ አድርገን ታሪካችንን እናድስ፡ የምንችለውን እናድርግ ወገኖቻችንን እና አካባቢያችንን እንርዳ።

አርጎባ ጀበርት፤- እስካሁን በነበራችሁ ጉዞ የሚያመሰግኑት አካላት ካሉ ዕድሉን እንስጥዎት

አቶ ሰይዱ፣ መጀመሪያ ማመስገን የምፈልገው ቤተሠቦቼን ነው።ይሔን ነገር የጀመርኩት ከቤተሰብ ነው ከወንድም ከእህት ከእህስት ነው የመጀመሪያውን እርምጃ ከጎኔ በማድረግ የጀመርኩት ከነሱ ነው። ወደ እንቅስቃሴ በሞራል እንድገባ ያደረገኝ የነሱ ድጋፍ ነው። በመቀጠል ሌሎች ዘመዶቼ ካናዳ አሉኝ ።አላህ ይጨመርላቸው! አውስራትሊያ፣ አውሮፓ ፣ ካናዳ እና አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ያሉ ዘመዶቼ እና ሌሎች የቅርብ ሰዎች ትልቅ የሞራል ስንቅ ሆነውኛል። ፣በተለይ ከአውስትራሊያ የአህመዴን ቤተሰብ፣ እና መህዲ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ከካናዳ ደግሞ የመሀመድ አህመድ ቤተሰቦች፣ የእነ ኢና ቤተሰብ እና የአደም አብድሰመድ ቤተሰቦች ብዙ አስተዋፅኦ አድርገዋል። በተጨማሪም ሌሎች ከአርጎባ ብሔር ውጪ የሆኑ እህቶች እና ወንድሞችን አሉን። እነሱም ከጎናችን ቆመዋል እና ያው ብዙ ስለሆኑ ስም ባልጠራም እዚህ ጋር ግን ከሰኡዲ እና ከዱባይ ካላችው ላይ በማካፈል ወንድማችን ኡመር በጣም ብዙ ረድቶኛል የሱፍ፣ሀሰን ትልቁን ሚና ተጫውቷል ።ወደፊትም በዚሁ ዙሪያ ብዙ የምንሰራቸው ስራዎች ይኖሩናል። ሌላው ከአሜሪካ ሶፊያ እህታችንን በጣም ነው የማመሰግናት በሞያዋ እና በገንዘቧ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጋለች እሷን ማመስገን እፈልጋለሁ። እነዚህ ከላይ የጠራኋቸው ሰዎች ሁሉ እኔ ሳልሆን እነ ሱናችው ትልቅ ድጋፍ ያደረጉት፡ ወደ ሀገር ውስጥ ስንመጣ ሸዋሮቢት ላይ ሸሁ ሲራጅ፣ ሸሪፍ እህታችን ፈቲያ፣ሌላው ደግሞ አቡበከር አልዩ አምባ ላይ እንዲሁም መጠቅለያ፣ ጋችኒ ላይ ትልቅ ድጋፍ ያደረጉልን አካላት እንዲሁም ሷሊህ በጣም ረድቶናል። ሁሉንም ከልብ አመሰግናለሁ። ሌላው ከሀገር ውስጥ ከጎኔ ሳይለይ ብዙ ሚና ሲያቀልልኝ የነበረው ሰኢድ መሀመድ ዘይን ዘመዴም ጓደኛም ጭምር ነው። ትልቁን ስራ የያዘልኝ እሱ ነው። አላህ ይጨምርለት ከሚዲያ ደግሞ OBN የሚዲያ ሽፋን በመስጠት ተባብሮናል። ሁሉንም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ ለማለት እወዳለሁ።

የይፋት ሱልጣኔት እና ወሳስማ ስርወ መንግሥት፡
በዘመን ተሻጋሪ እና ቅብብሎሽ የታሪክ እሴቶቻቸው
የሚታወቁ የኢትዮጵያ ፈርጦች!

ዘመነወርቅ ዮሐንስ (ዶ/ር)

ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ
ማህበራዊ ሳይንስ እና ስነሰብ ኮሌጅ
ታሪክ እና ቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል



የይፋት ሱልጣኔት

የይፋት ሱልጣኔት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ቀጠና በመካከለኛው የታሪክ ዘመን ወቅት የተመሰረተ ሀገርኛ መንግሥት ነበር። ምስረታውም ከሰሎሞናውያኑ ደገኛ መንግሥት ጋር በተመሳሳይ ወቅት በአስራ ሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ አካባቢ ተካሂዷል። የሱልጣኔቱ መስራች ዑመር ቢን ዱንያሁዝ አል-ወላስሚ ይባላል። የዚህ ሰው ስመ አመጣጥ ታሪክ ልዩ ልዩ ቅርጾች አሉት። በተመሳሳይም የይፋት ሱልጣኔት ስም በተለያዩ ቋንቋዎች የተለያየ መጠርያ ነበረው። ይህ ሱልጣኔት በረጅም ዘመን ታሪኩ በምስራቃዊው የኢትዮጵያ ቆላማ አካባቢዎች ውስጥ ይኖር በነበረው በአርብቶ አደሩ ህዝብ እና ደጋማ አካባቢዎች በነበሩት አርሶ አደሮች መካከል የኢኮኖሚ ዋልታ እና መገናኛ አውታር ሆኖ ለዘመናት አገልግሏል። የይፋት ሱልጣኔት የተመሰረተበት መልክዓ ምድራዊ ቀጠና ወደ ቀይ ባህር፣ ኤደን ባህረ ሰላጤ እና ህንድ ውቅያኖስ የሚወስዱ የንግድ መስመሮች የሚገናኙበት አካባቢ ነበር። በዚህም ምክንያት የውስጥ እና ውጭ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ መስተጋብሮች ተካሂደውበታል።

የይፋት ሀገርኛ ሙስሊም መንግሥት ከእሱ በፊት አስቀድሞ ተመስርቶ ከነበረው እህት የሸዋ ማክዙማይት ሱልጣኔት ጋር ቅርብ ትስስር ነበረው። ታሪካዊ ሁነቱ በእጅጉ የተሳለጠ ሁለንተናዊ ግንኙነትን ባህሉ እና መለያው አድርጎ ለዘመናት እንዲቆይ አግዞታል። ይህም በተለይ ከአስራ ሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ አስራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሳይቋረጥ በተከታታይነት ዘልቋል። የይፋት ሱልጣኔት ሀገርኛ መንግሥት ተጽዕኖ ከሀገር አልፎ በሌሎች የዓለም ክፍሎችም ታውቋል። በተለይ የተቀላጠፈ የንግድ እንቅስቀሴው ትልቅ ስም ያሰጠው ትውፊቱ ነበር። ከዚህ ነጥብ በመነሳት የይፋት ሀገርኛ ሙስሊም መንግሥት እስከ ዜይላ ወደብ ወይም የባህር በር ድረስ ይደርስ የነበረ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ሰፊ መልክዓ ምድራዊ ቀጠና ውስጥ የተለያየ ቋንቋ፣ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ የነበረው ህዝብ በአንድ ላይ ይኖር ነበር። ከዚህ አኳያ የይፋትን ሙስሊም መንግሥት የተሳስቦ መኖር ተምሳሌነት እና ታሪክ መማርያ መድረክ አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

በረጅም ዘመን የአስተዳደር ታሪካቸው ውስጥ የይፋት ሱልጣኔት መሪዎች ልዩ ልዩ መጠር
ማዕረግ ነበራቸው። በአስራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩት ዐጼ አምደ ጽዮን ዘመ
መንግሥት "አምበል" ፣ ከመቶ ዓመታት በኋላ በአስራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐጼ
ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት "ቃጥ" ፣ እንዲሁም በዐጼ በዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት በሱልጣኔቱ
መስራች ኡመር ቢን ዱንያሁዝ አል-ወላስሚ ስም "ወላስማ" የሚል የአስተዳዳሪነት መጠርያ
ማዕረግ ነበራቸው። የይፋትን ሙስሊም ሱልጣኔት አስደናቂ ከሚያደርጉት ታሪካዊ እሴቶቹ ውስጥ
አንዱ ይህንን ዓይነቱን አሻራ ለዘመናት ጠብቆ እና ተንከባክቦ ማቆየቱ ነው። በዘመናችን ይህንን
ዝንቅ ባህል ከሚያሳዩ ባህል፣ ወግ እና ልማድ ውስጥ አንዱ ወላስማ የሚለውን ስም የመጠርያ
ስማቸው ያደረጉ አባቶች በተለያዩ አካባቢዎች መኖራቸው ነው። ለምሳሌም በአልዩ አምባ ከተማ
የሚገኙትን አቶ አቡ ወላስማ እና የወላጅ ቤተሰቦቻቸውን ባህል አክባሪነት በአንክሮ ማስተዋል
ያስፈልጋል። ለወላስማ እሴት ዘመን ተሻጋሪነት እና የታሪክ ቅብብሎሽ ምን ያህል ትኩረት
እንደሰጡ ያሳያል። ከበርካታ የወላስማ ጠቃሚ አሻራዎች ውስጥ ይህንን ትውፊት ነው ዘመን
ተሻጋሪ እና ድንቅ የታሪክ ቅብብሎሽ ባለቤት ነው ብለን የምንለው።

የወላስማ ስርወ መንግሥት

ይህ ስርወ መንግሥት ለዘመናት በአስተዳዳሪነት በቆየባቸው ረጅም ዘመናት ውስጥ በተለያዩ
ቋንቋዎች ልዩ ልዩ መጠርያዎች ነበሩት። ይህ ስርወ መንግሥት በኢትዮጵያዊነት እሴት የኖረ
የሙስሊም ስርወ መንግስት ሲሆን ይፋት ውስጥ ከአስራ ሶስተኛው እስከ አስራ ስድስተኛው መቶ
ክፍለ ዘመን ስልጣን ላይ ቆይቷል። ከወላስማ ስርወ መንግሥት በፊት እና በኋላ በተከታታይነት
ሳይቋረጡ የቀጠሉ ድንቅ ሁለንተናዊ ትውፊቶች ነበሩ። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው
የሹመቾቹ መጠርያ ማዕረግ ነው። ይህ ማዕረግ ከደገኛው ሰሎሞናዊ ክርስቲያን መንግሥት
መሪዎች ጋር ተመሳሳይ ነበር። ለአብነት ያክል "አረድ" የሚለውን መጠርያ ማዕረግ ማንሳት
እንችላለን። የሰሎሞናውያኑን ደገኛ ክርስቲያን ንጉሥ የዐጼ ሰይፈ አረድ እና የይፋቱን ወላስማ
አህመድ ሃርብ አረድ ስመ ስያሜ ማየት በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የነበረውን ቅርበት እና መናበብ
ያስረዳል። ይህ በምሳሌነት የተጠቀሰ ድንቅ ታሪካዊ ትውፊቱ ማሳያ እንጅ ብቸኛው አይደለም።

በይፋት ወላስማ ስርወ መንግሥት መሪዎች እና በዐጼ በዕደ ማርያም መካከል የነበረው
ግንኙነት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ታሪካዊ ትውፊት ማስቀጠያ ባህል አድርጎ መውሰድ ያስችላል።
በሁለቱ መካከል በነበረው መልካም ግንኙነት ንጉሠ ነገሥቱ ለይፋት ገዥነት ወላስማ የሚለውን
ማዕረግ ለመጀመርያ ጊዜ እውቅና ሰጥተውታል። ይህ ትውፊት የዘመናት ፍሰት ሳይገድበው ረጅም
ዘመናትን የዘለቀ ሃገርኛ እሴት ሆኖ ኖሯል፤ ይኖራልም። "የይፋት ወላስማ" በበኩሉ ከአጎራባቹ
የአካባቢው ደገኛ ሰለሞናዊ መንግሥት ጋር ተስማምቶ እና ተከባብሮ የመኖርን አስፈላጊነት
እውቅና ሰጥቷል።

ዚህ በላይ በተገለጸው ትውፊት አማካኝነት ለዘመናት የቆየ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ ...
ስርወ መንግሥት የአስተዳደር ዘመናት ወላስማ መሀመዱ የይፋት አካባቢ ዋና አስተዳዳሪ እና
ነዋውያኑ ቤተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ሞገስ ያገኘ መልካም አስተዳዳሪ ነበር። ለአንድ መንግሥት ስፅናቱ
፣ ንግድ እና ኢኮኖሚ ዋና መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ሁለቱ ወገኖች ከነበራቸው ቅርበት እና ትስስር አኳያ
እና ኢኮኖሚ ነክ ጉዳዮች በበላይነት የተሰጡት ለወላስማ መሀመዱ ነበር። ዋና መቀመጫውም
በር አካባቢ ጎንች በሚባለው ስፍራ ነበር።

ይህ ትስስር የሸዋ ስርወ መንግሥት ከፍተኛ የእድገት ደረጃ በደረሰበት በአሰራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ
ነ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በሰፊው ተስተውሏል። በዘመኑ በተለያየ እርከን የነበሩ
ነሞች በንጉሡ ውሳኔ ሥልጣናቸውን እንደያዙ በወላስማ መሀመዱ ስር ሆነው አካባቢያቸውን
ጂያስተዳድሩ እውቅና ተቸሯቸዋል።።።

ለማጠቃለል ያህል በየዘመናቱ በተለያዩ ምክንያቶች ልዩ ልዩ ችግሮች ይከሰቱ ነበር። ነገር ግን ለዘመናት
ኖረው አብሮ የመኖር ትውፊት ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ አስከብሮ የድንቅ ባህል እና ትውፊት
ውቅያኖስ አድርጎ እንድትታወቅ አድርጓል። ከዚህ በላይ የተመለከትነው የይፋት ሱልጣኔት እና የወላስማ
ስርወ መንግሥት ታሪካዊ አሻራ አንኳር ማሳያ ነው። እኛም በዘመናችን ከሁለቱ የሃገር ሃብቶች መልካም
እሴቶችን ተምረን የይፋት ሱልጣኔትን፣ የወላስማ ስርወ መንግሥትን እና የደገኛውን ሰሎሞናዊ ክርስቲያን
መንግሥት መልካም አሻራ ተንከባክበን መጠበቅ፤ ለትውልድ ማስተላለፍ ይኖርብናል።

የታዋቂ ሙስሊም አባቶች ልዩ ልዩ ምክሮች ሲታወሱ (ሲዘከሩ)

ከዚህ በላይ እንደተጠቆመው በሸዋ ንጉሣውያን ቤተሰቦች እና በወላስማ መሀመዱ መካከል መልካም
ግንኙነት እንደነበረ ተወስቷል። ይህ ታሪካዊ ሁነት ሸሪፍ መሀመድ እና ሸሪፍ አህመድ ከመምህር ወልደ
ጊዮርጊስ እና መምህር ወልደ ዮሐንስ አስፋው እንዲሁም ከመምህር ሀይለ ሚካኤል ኢያሱ ጋር ሆነው ከጻፉት
የእጅ ጽሑፍ ላይ ይገኛል። ሰነዱ በአሁኑ ሰዓት በአርጎባ ልዩ ወረዳ ጋቾኔ ከተማ በሚኖሩት አቶ መሀመድ
አቡበከር እጅ ይገኛል። የጽሁፉ ይዘት የሚያተኩረው አንድነት፣ ፍቅር፣ መተሳሰብ እና መልካም ስብዕና ላይ
ነው። ይህ ታሪካዊ የእጅ ጽሑፍ "የዐጼ ስብስቴ፣ ወላስማ መሀመዱ እና የሰይድ ፈቂ አህመድ መረጭ ታሪክ
እና ትንቢት" በሚል አርእስት ተቃኝቷል።

በጽሁፉ ውስጥ የተጠቀሱ ነጥቦች ከሸዋ ስርወ መንግሥት ታሪክ ጋር የተያያዙ ጭብጦች ሲኖሩት
ከዚህ እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ። መርዕድ አዝማች ስብስትያኖስ አባቱ አቤቶ ነጋሢ ክርስቶስ
ካረፈ እና በአባቱ ዙፋን ላይ በተቀመጠበት ወቅት ሰይድ ፈቂ አህመድ ለወገኖቻቸው የወላስማ
ቤተሰቦች የስብስቴ ንግሥና ከፈጣሪ የታዘዘ መሆኑን ያስገነዝባሉ። አያይዘውም ስብስቴ ብቻ
ሳይሆን ቤተሰቡ ሁሉ ነጋሢ ነው፤ አትንኩት፣ አትተናኮሉት ብለው አባታዊ ምክራቸውን
አስተላለፉ። ይህንን ታሪክ የሰማው ስብስቴ ወደ ፈቂ አህመድ እንዲወስደው ለወላስማ መሀመዱ
ጥያቄ አቀረበለት። ወላስማ መሀመዱም ስብስቴን ከሰይድ ፈቂ አህመድ ዘንድ ወሰደው። ስብስቴ
እና ሰይድ ፈቂ አህመድ በተገናኙበት ሰይድ ፈቂ አህመድ የሚከተለውን ምክረ ሃሳብ ለገሱ።
"እናንተ በብልሃት እኔ በጸሎት ከተጋገዝን ከተደጋገፍን ከአድማስ ማዶ እንዘልቃለን" ስለዚህ
"ስብስቴ ደጋውን፤ መሀመዱ ቆላውን ይዛችሁ አስተዳድሩ" ብለው ምክራቸውን ሰጥተው
አሰናበቷቸው። በተሰጠው ምክረ ሃሳብ መሰረት ስብስቴ እና ወላስማ መሀመዱ ስራቸውን ጀመሩ
ይላል ይህ ሰነድ። ከዚህ የምንማረው ትምህርት ከእድሜ ባለጸጋ አባቶች የሚሰጥ ምክርን
የመቀበል ትውፊትን ነው።

መርዕድ አዝማች ስብስቴ በበኩሉ ይህንን ምክር ከተቀበለ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ትዕዛዝ አስተላለፈ፤ "ለሰይድ ፈቂ አህመድ በዚህ አቅራቢያ ያለውን መሬት ሁሉ ሰጥቻለሁ" ብሎ ሲናገር ሰይድ ፈቂ አህመድ "አይ እኔ ይሄ ሁሉ መሬት አያስፈልገኝም እኔ የምፈልገው አንድ መስጊድ መስሪያ እና ሰው አርሶ የሚበላበት መሬት ብቻ ነው፤ ሰፊ የመሬት ግዛት የሚያስፈልገው ለወላስማ መሀመዴ ወገን ነው" ብለው መልስ ሰጡ። መርዕድ አዝማች ስብስቴ በበኩሉ እንደዚያ ከሆነ "ከእያንዳንዱ የመለኮች መሬት አንድ አምስተኛ ግብር ለሰይድ ፈቂ አህመድ ስጡ" ብሎ ለወላስማ መሀመዴ በለዋጅ ትዕዛዝ አስተላለፈ" መሬቱም ተከፍሎ የወቅፍ ወይም ሰሞነኛ መሬት ተብሎ ግብር የሚሰበሰብበት የጸሎት ወቅፍ ወይም ሰሞነኛ መሬት ይሆን ዘንድ ለሰይድ ፈቂ አህመድ ተሰጣቸው። ተያይዞም በየሳምንቱ ረቡዕ ለመንግሥት ጸሎት የማድረጊያ ቀን ወይም የኒቃ ቀን ተብሎ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ታወጀ። ግብሩም የወቅፍ ወይም ሰሞነኛ መሬት ተብሎ ከተመደበው ይዞታ ላይ አንድ አምስተኛ እየተባለ መሰብሰብ ተጀመረ።

ከዚህ በመቀጠል ሰይድ ፈቂ አህመድ ስብስቴን እና ወላስማ መሀመዴን አንድ ላይ አስቀምጠው ትንቢት ተናገሩ። "ከእነ ልጅ ልጆቻችሁ ብትለያዩ አይቀናችሁም፤ መንግሥታችሁም አይበረታም፤ የመሀመዴ ወገን የሌለበት ጦር ድል ይሆናል ።ከብዙ የጦር መሰርያ የአንድ መሀመዴ ወገን ይበልጣል። ስለዚህ ልጆቻችሁ እና የልጅ ልጆቻችሁ እንዲጠነቀቁ ሁለት ጉዳዮችን እንዲያከብሩ አሳስቢቸው" ብለው መከሩ። እነዚህ ሁለት ጉዳዮች የተባሉትም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው። እነሱም፡-

1. "ስብስቴ ዘርህ እየበዛ፤ እየሰፋህ ትሄዳለህ ትረባለህ የእስላም ሀይማኖትን እንዳትነካ"
2. "እንተም መሀመዴ ወደፊት ታድጋለህ፤ ምንም ብታድግ አልጋ አትፈልግ።"

እነዚህን ትዕዛዞች ካስተላለፉ በኋላ መሃላ አማምለው አሰናበቷቸው።

በሌላ ጊዜ ለስብስቴ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ሌላኛውን ትንቢታቸውን ነገሩት። "እኔ ገና ስመጣ ዘጠኝ የወርቅ ማረሻ ከሆድህ ሲወጣ አይቻለሁ። እነዚህ ማረሻዎች ወርቅ መሆናቸው ንግሥናህ ነው፤ ማረሻ መሆናቸው ደግሞ ሀገር አቅኝ መሆንህን ለማሳየት ነው። ቁጥራቸውም ከአንተ ጋር አስር ነው። ከአስሩ በአንዱ ዘመን የተናገርነውን የሚያጎድል ሰው ይመጣል ተከታትሎም የውጭ ሃይል ሀገራችንን ይወራል፤ ግን አይቀናውም። ስለዚህ የመለያየት መንፈስ በመካከላችሁ እንዳይገባ ብለው ተናገሩ።"

የአስሩን ትውልዶች መቀመጫ ከተማ አስመልክተው "ሲናገሩ ሰባቱ ትውልድ መቀመጫቸውን አንኮበር ያደርጋሉ፤ ኋላ ጊዜ ግን ከአንኮበር ተነስተው ሌላ ቦታ ይሄዳሉ። ከዚህ በኋላ አንኮበር አባት ሀገር መሆኑ ይረሳል።" ስብስቴ በበኩሉ "ከአስረኛው ትውልድ በኋላ ምን ይሆናል? " ቢላቸው ሰይድ ፈቂ አህመድ አልቅሰው እና አዝነው "በመሬት ከመኖር በውስጢ መኖር (መሞት) ይሻላል" ብለው ነገሩት። አከታትለውም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን የግጥም ይዘት ያለውን ሌላ ትንቢት ነገሩት።

አንኮበር ዳገቷ፤ ሸንጉርጉሯ ሀገር፤
ንፋሷ መድሃኒት ለብዙ ነገር።
የመሀመዴ ወገን ሲቀርባት ከእርሷ፤
መዋረዱ አይቀርም በጭራሽ መፍረሷ።
እሷ ስትዋረድ እምብዛም አያምር፤
ምንም ደስ አይለውም የመንግሥትየው ዘር።
የዘመኑ ንጉሥ በነገሩ ቢያውቅ፤
የመሀመዴን ወገን እቅርቦ ከሩቅ፤
አንኮበርን ማደስ በጣም እንድትደምቅ፤
ካስረኛው ንጉሥ ምናለባት ብትዘልቅ።

በመለኮች (በሰማይ) ሀገር አንድ ወሬ ይወራል
አስረኛው ንጉሥ ሶስት ጡንዲል (ቀንዲል ሻማ የሚመስል) ያበራል፤
ዓለምን ለማየት በእሱ ይጣጣራል፤
ሃሳቡን ሳያደርስ አንደኛው ይጠፋል፤
በሁለቱ መብራት ብርሃኑ ይፈዛል፤
እንኪን ዓለም ሊያሳይ ለዚያውም ይሰንፋል።
ለዚህማ ጉዳይ ዋናው መድሃኒት፤
እስፍራው መመለስ የወቅፍን መሬት፤
አንኮበርን ማደስ ማድረግ እንደጥንት፤
የመሀመዴን ወገን ማዕረግ መስጠት።
ልንገርህ ስብስቴ ከፍ ያለ ምክር፤
ትፈልግ እንደሆን ለልጅ ልጅ መኖር፤
የመሃላህን ነገር በጣም አጠንክር፤
መኖርያ ሃገራችሁ ይሁን አንኮበር።
ከአስረኛው ወዲያ የሚመጣው ግዛት፤
እጅግ በመሰልጠን በትምህርት ብዛት፤
ንጉሥ ይቀርና በግንፈላ መግዛት።
ውስጣዊ ንግግር ወሬ ያመነጫል፤
ግልጹን ነገር ብንናገር ነገሩ ይረጫል፤
ሰው በሰማይ ወጥቶ ከኮከብ ይጋጫል፤
ከአስረኛው ወዲያ መቼ ደስ ያሰኛል።
አደረብኝ እንጂ ፍርሃተ እግዚአብሔር፤
ምድር ሰማይ እስኪያልፍ ያለውን ነገር፤
እነግርህ ነበረ ምንም ሳላስቀር፤
እንግዲህ እንተወው ባጭሩ ይብቃን፤
መቼ ደስ ያሰኛል የሚመጣው ቀን።

ማሳሰቢያ፡- ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ግጥመ ትንቢት ከእጅ ጽሁፍ ሰነዱ ላይ በቀጥታ የተወሰደ ነው። መልእክቱም መሃላ የማክበር አስፈላጊነትን፣ መደማመጥን፣ መከባበርን፣ ታሪክ፣ ትውፊት፣ ቅርስ መጠበቅ ማስጠበቅ እና ለትውልድ ማስተላለፍ አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል። ከዚህ ቀጥሎ በተለያየ ጊዜ እና ቦታ ሙስሊም የሃይማኖት አባቶች ስለ አርጎባ፣ ወለስማ፣ ይፋት እንዲሁም መሰል ታሪካዊ ጉዳዮች ዙርያ ያስተላለፉትን የበሰለ መልዕክት እንመልከት። ታዋቂው ሼክ ሙሀመድ ሳላህ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ታሪካዊ ሁነት ዙርያ የሚከተለውን መልዕክት አስተላልፈዋል።

በኢፋት፣ ወለስማ ከኡላማ፣ ኡላማ ከቆፋሪው ጋር አብረው ታልሰሩ፣ ቆፋሪው ለአጣሪው እና ለሲራራው ካላቀበለ፣ በኃይማኖት እንድ ሆነው ቢገኙም መስጊድ ተወለስማው እለፍኝ ጋር ቋንቋ ተሌላት፣ እንዴት ኢፋት ኢፋት ይሆን ነበር። ቄሱና ንጉሡ፣ የተቆራኙት በዚሁ መንገድ ነበር። አንዱ ለአንዱ መከታ እንደተጓጓኑ መዘንጋት አይገባም።

ሌላኛው ሙስሊም አባት አል ሀጅ መሀመድ ኑር ሳላህ በበኩላቸው እንዲህ ብለዋል።

በአርጎቦች ዘንድ አብሮ መስራት በአርሻ ጊዜ እና በአጨዳ ጊዜ በሚስተዋለው የአብሮ መስራት ብቻ አይደለም። ኃይማኖታዊ እና ትምህርታዊ ስራም ላይ ነው። ወላስሞች ከኡለማዎቹ ጋር አድርገውት የነበረው ይህንኑ ነበር።

ሼክ ኑር ሁሴን ዑመርም ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ድንቅ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዛሬ፣ ዛሬ ሁሉም የአርጎባን ጉዳይ አውቃለሁ ባይ ነው። እውነቱን ግን ከያዝን እያውቁትም። እንዲያውቁ ከተፈለገ ከሚያውቁት መረዳት ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ስንቱ አላዋቂ በአርጎባ ታሪክ ላይ አዋቂ እየሆነ ነው። አርጎባን ወላስማ ብለውታል። በጭራሽ በጭራሽ ወላስማም አርጎባ ማለት አዶለም። አርጎባ እንዲሁ። ለየቅል ናቸው። ወላስማነት ማዕረግ ነው ሹመት ነው በውርስም አርጎባነት ሀዝብነት ነው መገለጫ ነው ማንነት ነው።

በተመሳሳይ ሼክ ሙሀመድ ሳላህ ከዚህ በታች ያለውን አስተምሯቸውን ለማሰዋል።

በዚህ ዓለም ላይ የሆነው ጉዳይ ሁሉ ቋሚ ሆኖ አይቀጥልም። እንደዚሁ ዛሬያ ኢፋትነትም ወላስማነትም አርጎባነትም እንደነበሩ ሆኖ አልቀጠሉም። ተመልከት የአርጎቦች ቁንቋም እንደድሮው አይደለም። ብዙ ብዙ ተለወጠ። ከድሮ እስከአሁኑ በይፋት ወላስማነት ለአርጎቦች ነበር። ዶባዎች አርጎብነት ጋር ተዋሀደው ወላስማ ከመሆን የከለከላቸው አልነበረም። በኢፋት ግዛት አንዴ ወላስማ አንዴ አንበል አንዴም ቃጥ ተመልሶም የተሸረሸረው ወላስማ በአርጎቦች ዘንድ ዛሬም እገሌ ወላስማ ይባላል። ተመዓረግነት ያልተሻገረ እንደድሮ ያልጠነከረ። ይህንን ዓይነት ጥያቄ ለመዘርዘር ወደ ሲልሲላው ወደ መናቂብ-መናቂባው እያስሄደንም። ያ ዓይነቱ ጋ ስንሄድ ጥልቁን የኢፋትና የወላስማዎች ጉዳይ ከሌላው ግንኙነት ጋር ቲያያዝ ነው። ለእኛ ለእኛውማ ገበሬዎች ነን፣ ወታደሮች ነን ጉዳዩን ለመዘርዘር የፊተኞች የኛ ምንጅላቶች ብለው ብለውት ሄደዋል። እኛ ከነሱ ወስደን እየሄድንበት ነው።

ማስታወሻ

እነዚህ የታዋቂ ሙስሊም አባቶች የታሪክ፣ የባህል፣ የወግ፣ የልማድ፣ ትውስታ፣ ስብስቦች የተገኙት ከዶክተር አህመድ ሀሰን ዑመር ልዩ ልዩ ስራዎች ነው። በስተመጨረሻ የተጠቀሰው መልዕክትም ከእኒህ ምሁር ቤተሰቦች የተገኘ ነው።

የአርጎባ ቅርሶች

አህመድ አገር መስጂድ

አህመድ አገር መስጊድ በጨኖ የሚገኝ እድሜ ጠገብ ከሆኑት መስጊዶች መካከል አንዱ ነው። መስጊዱ በትናንሽ ድንጋዮች የተሰራ ጣሪያውም የእንጨት እርብራብና አፈር የተደለደለበት በመሆኑ በአካባቢው ከሚገኙ መስጂዶች ለየት ያደርገዋል። ውስጣዊ ገጽታው ወፍራምና ጠንካራ የሆኑ 21 ምሰሶዎች ያሉት ሲሆን ይህ መስጂድ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አገልግሎት ይሰጥ እንደነበረ የሀገር ሽማግሌዎች ያስረዳሉ። መስጂዱ ከ1300 ዓመት በላይ እንዳስቆጠረ የታሪክ አስረጂዎች ይናገራሉ። የመስጂዱ ስፋት 10.50-11.50 ሜትር ቁመቱ በውጭ በኩል 3.10 ሜትር ሲሆን በውስጥ በኩል ደግሞ 2.9 ሜትር ነው። ስፋታቸው 80-70 ሳ.ሜ. የሆኑ ሁለት መስኮቶች ያሉት ሲሆን በመስጂዱ የውስጥ ግድግዳ ገባ ብሎ የተዘጋጀ የመጽሀፍ መደርደሪያ ጣቄት አለው።



የመለሳይ አገር መስጂድ

የመለሳይ አገር መስጂድ የኢማም አህመድ መነሻ የሆኑት የመለሳዮች ጎሳ በ788 ዓመተ ሂጅራ የመሰረቱት እንደሆነ ይነገርለታል። መለሳይ አገር የሚባለው መስጊድ ከፍታ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ፣ ብዙ የድንጋይ ቤት ፍርስራሽ በአቅራቢያው ይገኛል። መስጊዱ ከ1300 ዓመት በላይ እንዳስቆጠረ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። የመስጊዱም ስፋት 24 ሜትር ሲሆን 3.3 ሜትር ቁመት ነበረው። እስከአሁን ድረስ የመለሳይ ጎሳ ባላባትነቱን ይዞ የቆየ እንደሆነ የማህበረሰቡ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።





የኖራ መስጂድ



የኖራ መንደር ከአዲስ አበባ በስተሰሜን 300 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ቀወት ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የአርጎቦች ቅርስ የሆነ ልዩ ቦታ ነው:: በ2002 እ.ኤ.አ አቆጣጠር ከፈረንሳይ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተወጣጡ ሙሁራን አማካኝነት በቁፋሮ የተገኘ የመካከለኛው ዘመን መንደር እንደነበር ይነገርለታል:: በ13ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ እንደተቆረቆረ የሚነገርለት ይህ መንደር በአራት ስርወ መንግስቶች ውስጥ ገናና ከነበሩ መንደሮች የመጀመሪያው ነው:: ከነዚህ በተጨማሪ ከኢፋት የጥንት ከተሞች ከነበሩት መካከል ጀለቦ እና ጀበርቲ በአፋር ክልል አርጎባ ልዩ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የቀደምት የኢፋት ከተሞች መካከል እንደሆኑ አካባቢው ላይ ቅሪት አሻራዎች ያመላክታሉ:: ተጨማሪም ከአርጎባ ልዩ ወረዳ አዋሳኝ አካባቢ የሚገኙት አልዩ አምባ እና ብቅልዘር (መቶምንጭ) የይፋት ስርወ መንግስት ከተሞች መካከል እንደሆኑ የሚታወቅ ነው::

የጎዜ መስጂድ

የጎዜ መስጂድ ከሸዋ ሮቢት ከተማ በስተሰሜን በኩል በ8ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል:: በጎዜ መስጊድ ዙሪያ ተፅፎ በተገኘ መረጃ መሰረት 110 ዓመተ ሂጅራ እንደተሰራ ያመለክታል:: የጎዜ መስጂድ ሀገረኛ የኪነ ህንፃ ጥበብ የፈሰሰበት ታላቅ መንፈሳዊ ቦታ ነው:: የመስጅዱ ስፋት 7 ሜትር ገደማ ሲሆን ከምድር እስከ ጣሪያው ደግሞ 4 ሜትር አካባቢ ከፍታ አለው:: የጎዜ መስጂድ የእስልምና አስተምህሮ እና የልህቀት ማዕከል እንደነበር ይታወቃል::





እማ መዲና

በአርሶ ልዩ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ መስሪያቤት መሀከል የእማ መዲና መኀደር ማህጀድ አንዱ ነው። እማ መዲና አለም ሴት ነበሩ። ወንድማችው ከኢጣሊ ሀገር ከይተመለሱ በቅንጣታችው ሽውድደው (ሰፍሰው) ያመጡትን 10 ጥራዝ የሐይማኖት መፅሐፍ በእጃችው ፅረው ያነጋጀችው እማ መዲና እንደሆኑ ይገራራል። እማ መዲና አለም የፃፉትን የሐይማኖት መፅሐፍ በአሊቃ ሲያስመጣው ካለ እንዲት አናገቢ በስተቀር ስወሰት ሳይሸሰት በመቅረት አድናቆትን አትረፈው አስከሃሬ በአርሲያት ይሰከራሉ። በሌላ በኩል በሐሰን ወቅት የሚቀራ (የሚከበሩ) የፀሎት መፅሐፍ መዘጋጀታችው የሚታወቅ ነው።



አሊ ግንብ



የአሊ ግንብ በኢፋት ኡመር ወላስማ ስርወ መንግስት ልክ እንደ ባንክ ሆኖ ሲያገለግል የነበረ ሰው ሰራሽ ዋሻ ሲሆን መዝጊያው በድንጋይ ተጠርቦ የተሰራ ነው። አሊ ግንብ በተለይ ነስረዲን የተባለው የኡመር ወላስማ ልጅ መቀመጫ እንደነበር እና መንደሩ እስከአሁን ድረስ በነስረዲን የሚጠራ ሲሆን ከጋራው ዝቅ የሚል ቦታ ላይ ይገኛል። በዚህ ስፍራ ሌላው አስገራሚ ነገር ከመንደሩ መስጊድ እስከ አዋዲ ወንዝ ድረስ ተጠርቦ የተስተካከለ በድንጋይ ምንጣፍ የተነጠፈ ዘመናትን የተሻገረ ድንቅ ጥበብ ነው። የጋራው እና የዋሻው ክፍል አሊ ግንብ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን አሁንም ቦታው ላይ የመንደሩ ጥንታዊ መስጊድ ፍርስራሾች ይገኛሉ። የአሊ ግንብ በአርነባ ማህበረሰብ ትውፊት ውስጥ ልዩ ስፍራ አለው።

ሾንኬ

የሾንኬ መንደር በኦሮሚያ ብሄረሰብ አስተዳደር በዳዋ ጨፋ ወረዳ ጆሮታ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን በሰይድ ፈቂ አህመድ እና በሸህ ኩንሊባስ እንደተመሰረተች ይነገርላታል:: ሰይድ ፈቂ አህመድ እና ሸህ ኩንሊባስ ከአዘሉ በመነሳት ሾንኬ እና ጦለሀ መንደርን እንደመሰረቱ በአካባቢው ነዋሪዎች ይነገራል ፤ መቃብራቸውም በሾንኬ መንደር ይገኛል:: በሾንኬ መንደር ከጥንት ጀምሮ የሚኖሩት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ የአርጎባ ማህረሰብ እንደሆኑ የሚታወቅ ሲሆን የማህበረሰቡ ነዋሪዎች ቤታቸውን ለመገንባት ድንጋይ እና ሸክላ የተጠቀሙ ሲሆን ለእይታ በሚማርክ መልኩ የታነፁ ፣ ድንቅ በሆኑ ህንፃ ሙያተኞች የተሰራ እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው:: የሾንኬ መንደር በአለም አቀፍ ደረጃ በቅርስነት ሊመዘገብ የሚገባ የቀደምት ስልጣኔ መነሻ የአርጎቦች መንደር ነው::





ጥንታዊ መካነ መቃብሮች

በአፋር ክልል አርጎባ ልዩ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ የተለያዩ ምልክት ያረፈባቸው መካነ-መቃብር-ድንጋዮች (ጡሉል) ከ17-135 ዓመተ ሂጅራ የሚያመለክቱ ከመቃብር ላይ ድንጋዮች ተፈልፍለው የተቀረፁ ፅሁፎች ያስረዳሉ:: በነዚህ የመቃብር ላይ ድንጋዮች (ጡሉሎች) ሟች በህይወት ዘመኑ የነበረበትን ሁኔታ የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ ሟች ሴት ወይም ወንድ መሆናቸውንና እድሜአቸውን ፤የሟችን ስም እና የተለያዩ ማዕረግ ያላቸው መሆናቸውን ያመላክታሉ:: ከነዚህም መካከል:- ሐፊዝ፣ አሊም፣ ሙፍቲ፣ ወልይ፣ አገር አቅኚ መሆናቸውን የሚገልፁ ምልክቶች በመካነ-መቃብር ድንጋዮች (ጡሉል) ላይ ተፈልፍለው እና ተቀርፀው ይገኛሉ:: በሀገራችን ኢትዮጵያ ብሎም በአለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የጥናት ቡድኖች የቀደምት የእስልምና አሻራ ያረፈባቸውን ፅሁፍ ያለባቸውን የመቃብር ላይ ድንጋዮች ሊፈትሹ ይገባል::







እስላማዊ ቅርሶች ዓይነትና ስርጭት ከሰሜን ሸዋ እስከ ከደቡ ብወሎ

ዶ/ር ሐሰን ሰዒድ

ሐሰን መሐመድ

አዲስ አበባ 2008ዓ.ም.

ወቃሊም

ወቃሊም በአርጎባ ማህበረሰብ ዘንድ ተወዳጅ የምግብ አይነት ነው። አዘገጃጀቱ የበሬ አንጀት በጥሩ ሁኔታ ታጥቦ ከተዘጋጀ በኋላ የሙያው ባለቤት በሆነች የአርጎባ ሴት ደቀቅ ተደርጎ ተከትፎ የተከተፈውን ስጋ በጨው እና ከሰባት 7 በላይ ቅመማ ቅመሞችን በመጠቀም ታሽቶ ይዋሀዳል። በዚሁ ሁኔታ የተዘጋጀው «ወቃሊም» ገመድ ላይ ተንጠልጥሎ ደረቅ አንዲል ይደረጋል «ወቃሊም»ለ4 አመት ያክል ሳይበላሽ የሚቆይ ባህላዊ የምግብ አይነት ነው።የአርጎባ ማህበረሰብ በንግድና በሐጅ ጉዞ ላይ አይለያቸውም ነበር።

ወቃሊም



በሀረሪ ክልል የሚገኝ
የኮረሚ መንደር





በሀረሪ ክልል የሀመርዲን
መስጂድ



የአሁኗ ጊያቸንኔ /Present Gacheni



የወደፊቷ ጊያቸንኔ/The future Gacheni

